# የዜጎች መድረክ

ቅፅ2 ቁጥር 54 መስከረም 6 ቀን 2013 ዓ.ም
በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## ‹‹በያዝነው ዓመት የሚካሄደው ምርጫ ወደ ዴሞክራሲ ሽግግር የምናደርግበት ይሆናል የሚል ተስፋ አለኝ››

የሺዋስ አሰፋ የኢዜማ ሊቀመንበር



# ቆይታ

## ‹‹በያዝነው ዓመት የሚካሄደው ምርጫ ወደ ዴሞክራሲ ሽግግር የምናደርግበት ይሆናል የሚል ተስፋ አለኝ››

### የሺዋስ አሰፋ የኢዜማ ሊቀመንበር

## ‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ትልቁ ፕሮጀክት የዴሞክራሲ መሰረት መጣል ነው››

ከኢዜማ ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋ ጋር በፓርቲያቸው ያለፉት 1 ዓመት ከ4 ወራት እንቅስቃሴና ቀጣይ ዕቅድ እንዲሁም በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ጋር ሰፋ ያለ ቆይታ አድርገናል:: ይህንን ሰፋ ያለ ቆይታ እንድታነቡት እንጋብዛችኋለን:: መልካም ንባብ!



*ከእኛ ጋር ቆይታ ለማድረግ ፍቃደኛ ስለሆኑ በጣም እናመሰግናለን::*

እኔም አመሰግናለሁ::

*ኢዜማ ከተመሰረተ 1 ዓመት ከ 4 ወራት እንዳስቆጠረ ይታወቃል:: ያለፉት ዓመታት ጉዞ ምን ይመስል ነበር? በያዝነው የ2013 ዓ.ም የያዘው ዕቅድና ስትራቴጂስ ምን ይመስላል?*

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ጥሩ ወቅት ላይ ነው የምንገኘው:: በአመራሩም ሆነ ከአመራሩ ውጪ ያሳለፍነውን ሂደት ለመገምገም ሞክረናል:: ኢዜማ ወረዳን መሰረት ያደረገ አደረጃጀትና ማኅበራዊ ፍትህን የሚከተል የፖለቲካ ፓርቲ ሲሆን ይህንን አደረጃጀትና የፖለቲካ ፍልስናን የተቀበሉ 7 የፖለቲካ ፓርቲዎች የመሰረቱት ድርጅት ነው:: የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ራሳቸውን አክስመው ነው ኢዜማን ሊመሰርቱ የቻሉት:: ፓርቲዎቹ ኢዜማን ከመሰረቱ በኋላም 3 የፖለቲካ ፓርቲዎች ራሳቸውን አክስመው ኢዜማን ሊቀላቀሉ ችለዋል:: በአጠቃላይ 10 የፖለቲካ ፓርቲዎች ኢዜማን መስርተዋል ማለት ይቻላል:: ሁሉንም የሀገሪቱን ክፍሎች በአንድ ጊዜ ማዳረስ የቻልነውም በዚህ ምክንያት ነው :: ኢዜማ በሰው ሀይል፣ በፋይናንስ እና በፖሊሲ ሰነዶች ራሱን ያደራጀ በመሆኑ የፖለቲካ ፓርቲ ሲጠራ ከመጀመሪያው ረድፍ የሚቀመጥ ፓርቲ ነው::

ፓርቲው ከተመሰረተ 1 ዓመት ከ4 ወራት ብቻ ቢሆንም በውስጡ የሚገኙ ሰዎች በፖለቲካው ልምድን ያካበቱ እንደመሆናቸው መጠን ለኢትዮጵያ ፖለቲካ አዲስ ነው ማለት አይቻልም:: ለምዝገባ ነው አዲስ የሆነው እንጂ ለፖለቲካ ሜዳው አዲስ የሚባል አይደለም:: የኢትዮጵያን ፖለቲካ በደንብ የሚረዱ ሰዎች ያሉበት የፖለቲካ ፓርቲ ስብስብ ነው:: ወረዳ አደረጃጀትን መነሻ ከማድረግና ማኅበራዊ ፍትህን እንደ ፖለቲካ ፍልስፋና ከመከተል በተጨማሪ የስትራቴጂክ ሰነድ አዘጋጅተን ነው ሥራ የጀመርነው:: በስትራቴጂክ ሰነዳችን ላይ 4 መሠረታዊ ግቦች አሉ:: የፖለቲካ ፓርቲ መመስረት፣ የመንግሥት መዋቅር ማዘጋጀት፣ ለተቋማት ነፃነትና ለሠላምና መረጋጋት መስራት፣ ፍትሐዊ በሆነ ምርጫ ማሸነፍና በቂ የሆነ ወንበር በማግኘት ሀገር ማስተዳደር መቻል ግቦቻችን ናቸው::

ባለፉት 1 ዓመት ከ4 ወራት በእኛ ግምገማ ኃላፊነት የሚሰማው ጥሩ ተወዳዳሪ የሆነ ጠንካራ አደረጃጀት ያለው (435 የምርጫ ወረዳዎችን ማደራጀት ተችሏል) አስሩንም ክልሎችና ሁለቱን የከተማ አስተዳድሮች የሸፈነ የፖለቲካ ድርጅት መመስረት ችለናል :: ስለዚህም አንደኛውን ግብ (የፖለቲካ ፓርቲ መመስረት) አሳክተናል::

ለሠላምና መረጋጋት መስራት የሚለውን ሌላኛውን ግባችንን አሳክተናል የሚለውን ወደፊት የምንገመግመው ቢሆንም ኢዜማ፣ ኃላፊነት የሚሰማው የፖለቲካ ድርጅት በመሆኑ የፓርቲዎችን ስነ ምግባር ሰነድ ከማሰልጠን ጀምሮ በምንም አይነት የብጥብጥና ሁከት ጥሪ ባለመሳተፍ ሕዝብ በሚያየውና መንግሥትም በሚመሰክረው ደረጃ ለሰላምና መረጋጋት ሰርቷል::

ሌላኛው ግባችን የሆነው የመንግሥት መዋቅር በመዘርጋት ምርጫ ማሸነፍን በሚመለከት ወደፊት የሚታይ ይሆናል:: ያለፈውን ዓመት ሁለቱን ግቦቻችንን በማሳካት በጥሩ ስኬት አሳልፈነዋል የሚል እምነት አለኝ:: ባለፈው ዓመት ከምርጫ ቦርድ እውቅና ለማግኘት፣ ፅ/ቤት ለማግኘት፣ መዋቅር ለመዘርጋት፣ የፖሊሲ ሰነዶችን በማዘጋጀት፣ አባላትን በአስተሳሰብና በአሰራር ለማዋሀድ ረጅም ጊዜ ወስዶብናል:: ከቀደመው ጊዜ በተሻለ መልኩ ልንጓዝ የምንችልበት ወቅት ላይ ነው የምንገኘው:: ከዚህ ቀደም ፅ/ቤት በመክፈትና አባላትን በማደራጀት ነበር ጊዜ ስናጠፋ የቆየነው::

ከዚህ በኋላ ዘውግ ዘለል የሆኑ እንደ ወጣቶች ማኅበር፣ የሴቶች ማኅበር፣ የሙያ ማኅበራት ያሉ ለዴሞክራሲ መገንባት የሚያግዙ ተቋማትን በመቅረፅና አብሮ የመሥራት ዕቅድ አለን:: ባሳለፍነው ዓመት ባካሄድነው ግምገማችን እንደገለፅነውም ገዢው ፓርቲን ጨምሮ ዘውጋዊም ሆኑ ሕብረ ብሔራዊ አደረጃጀት ካላቸው ፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በጋራ በሚያሰሩ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ አብሮ ለመስራት ዕቅድ አለን:: የእያንዳንዱ ክፍል ዕቅድ፣ በስርአትና በበጀት ነው እየተንቀሳቀሰ ያለው:: ምንም ነገር ከዕቅድና ከስትራቴጂ ውጪ አይሰራም:: ባስቀመጥነው ዕቅድ መሰረት ነው ሥራችንን የምናከናውነው:: ቀጣዩ ዓመት ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ኢዜማም እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ለመጀመሪያ ጊዜ በምርጫ ወደ ዴሞክራሲ ሽግግር የምናደርግበት ይሆናል የሚል ተስፋ አለኝ::

*በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ከሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር አብሮ ለመስራት ዕቅድ እንዳላችሁ ቀደም ብለው ጠቅሰውልኛል:: ፓርቲዎም ለዚሁ ተግባር ሲል 5 አባላት ያሉት ኮሚቴ ማቋቋሙን አውቃለሁ:: ይህ ኮሚቴ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል?*

ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር አብሮ ለመስራት 5 አባለት ያሉት ኮሚቴ ማቋቋም ያስፈለገን ከግምገማችን የተነሳ ነው:: ሌሎች ፓርቲዎች ካልከሰሙ በስተቀር አብረን ልንሰራ እንደማንፈልግ ተደርጎ የሚገለፅ ነገር ነበር:: እኛ አንድም ቦታ እንደዚያ ብለን አናውቅም :: ምርጫ ለመወዳደር ብቻ አይደለም አብሮ የሚሰራው:: ሰላምና መረጋጋት፣ የሕግ የበላይነት፣ ሰብዓዊ መብት ላይ አብሮ መሥራት ይቻላል:: ይህንንም ለገዢው ፓርቲ ጨምሮ ለተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች በተለያየ ጊዜ ባገኘናቸው ጊዜ ገልፀንላቸዋል::

ያቋቋምነው ኮሚቴ ያለ ምንም ልዩነት ከተለያዩ ፓርቲዎች ጋር በመነጋገር ላይ ይገኛል:: ፓርቲዎቹ አላማቸው ምንድነው? ኢትዮጵያ ላይ ማምጣት የሚፈልጉት ምንድነው? ፕሮግራማቸው ምንድነው? ከኢዜማ ጋር ያላቸው ግንኙነትና ልዩነት ምን ይመስላል? የሚለውን እያጠና ይገኛል:: ይሄንንም በፈርጅ በፈርጅ እያደረገ

> ‹‹በመዋቅር ደረጃ ደግሞ እስከ ውህደት ድረስ አብረን የምንሰራቸው ድርጅቶች ካለ፣ እሱን በመለየት ለብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚያቀርብ ይሆናል::››

ያቀርብልናል:: ቀድም ብዬ እንዳነሳሁት በሰብዓዊ መብት ላይ አብረን የምንሰራቸው ድርጅቶች ይለያል:: በመዋቅር ደረጃ ደግሞ እስከ ውህደት ድረስ አብረን የምንሰራቸው ድርጅቶች ካለ፣ እሱን በመለየት ለብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚያቀርብ ይሆናል :: በቅርቡ ፅ/ቤታችንን ስናስመርቅ ሁሉንም የፖለቲካ ፓርቲዎች የምንጠራ ይሆናል :: ይህ የመጀመሪያው አይን ገላጭ የሆነ ግንኙነት ይሆናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን :: ምንም ልዩነት ሳናደርግ ምርጫ ቦርድ እውቅና የሰጣቸውን የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁላ እንጠራለን:: ለኢትዮጵያ በሚጠቅሙ ነገሮች ላይ በማኅበራዊ ሚድያው ላይ የሚጮኸውን ያህል ልዩነት እንደሌለን አይተናል:: ሁሉም ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ናቸው:: የየራሳቸው ሀሳብም አላቸው:: አንድ በሚያደርገን ላይ አብረን እንሰራለን:: አንድ በማያደርጉን ላይ ደግሞ በፖሊሲ እንወዳደርባቸዋለን:: ሕዝብም ፍርዱን ▶

## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

መስከረም 6 ቀን 20113 ዓ.ም
አዲስ አበባ

▶ ይሰጣል፡፡ የሕዝብን ፍርድም ሆነ ውሳኔ ለመቀበል ሁላችንም ዝግጁ መሆን አለብን፡፡ ኢዜማ፣ የሕዝብን ውሳኔ ለመቀበል ምንም ችግር የለበትም፡፡ ሕዝብ የመረጠውን ለመቀበል ዝግጁ መሆን አስፈላጊነት ላይ መስማማት ይኖርብናል፡፡

የካበተ ልምድ ያላቸው፣ ከሌላ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ጋር ጥሩ ግንኙነት ያላቸው ሰዎችን ያቋቋምነው ኮሚቴ እየመረጠ ነው፡፡ ሲሰሩ የቆዩትን ሥራና የደረሱበትን ውጤት ከወር በኋላ የሚያቀርቡ ይሆናል፡፡ በብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መሰረትም ከእያንዳንዱ ፓርቲ ጋር ጤናማ የሆነ ግንኙነት እንፈጥራለን የሚል እምነት አለኝ፡፡

*ባጠናቀቅነው የ2012 ዓ.ም ኢዜማ ራሴን መፈተሽ አለብኝ በሚል አንድ ግምገማ ማካሄዱ ይታወሳል፡፡ በግምገማቹህ ወቅት የተነሳ አንድ ነጥብን ተከትዬ ጥያቄ ማንሳት እፈልጋለሁ፡፡ ኢዜማ፣ ከገዢው ፓርቲ (ብልፅግና) ጋር ግንኙነት ፈጥሮ የሕዝቡን ጥያቄ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ አልፎታል የሚል ትችት ይሰነዘርበታል፡፡ ይህ ትችት እየተሰነዘረ ያለው በምን የተነሳ ነው ትላላቹህ? ይህንን ትችት ለማጥራትስ ምን ያህል ርቀት ተጉዘናል ብላቹህ ታስባላችሁ?*

ከግምገማችን መሀል አንዱ ነጥብ የነበረው ኢዜማ፣ በአባላቱ፣ በሚድያና በሕዝብ ዘንድ ምን አይነት ገፅታ አለው የሚል ነው፡፡ አላማችን ለትውልድ የሚተላለፍ በሀሳብ የበላይነት የሚያምን የፖለቲካ ድርጅት መመስረት እስከሆነ ድረስ ወደ ውስጥ በመመልከትግምገማ ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህም ግምገማ ስናካሄድ የፓርቲ አመራርና አባላት ብቻ አይደለም በግምገማው ተካፋይ እንዲሆኑ የተደረገው፡፡ ብዙ ጊዜ ራስን ስትገመግም ለራስ የማድላት ነገር ሊኖር ስለሚችል የውጪ ሰዎችንም ማካተት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ብለን ከውጪም ሰዎች አምጥተን ፓርቲውን አስገምግመናል፡፡

ከውስጥም ከውጪም ሲነሳ የነበረው አንዱ ጥያቄ ገዢው ፓርቲ ላይ ኢዜማ ያለው እምነት ነው፡፡ አንዳንዶቹ ትችቶች መሰረት የሌላቸው በማኅበራዊ ሚዲያው ላይ የሚዞሩ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ኢዜማን ሊለውጡና ሊያስተምሩ የሚችሉ አድርገን የወሰድናቸው ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ግምገማውን ተቀብለን እንዴት ነው ማስተካከል ያሉብን የሚለውን ተመልክተናል፡፡ ከሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር እንሰራለን የምንለውም ካካሄድነው ግምገማ የተነሳ ነው፡፡ ከገዢው ፓርቲ ጋር ብቻ ሳይሆን ሊያሰሩ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ከሁሉም ጋር አብረን እንሰራለን፡፡ ከገዢው ፓርቲ ጋር በተገናኘ በእኛ እምነት ለውጡ የገዢው ፓርቲ ብቻ ነው የሚል እምነት የለንም፡፡ ለውጡ የእኛም ጭምር ነው ብለን ነው የምናምነው፡፡ ለውጡን ቃሊቲ፣ ዝዋይ፣ ሸዋሮቢት፣ ማዕከላዊ የነበሩ ሰዎች አብረው ያመጡት ነው፡፡ ለውጡ በስርአት መሄድ አለበት፡፡ ለውጡ በስርአት እንዲሄድ ደግሞ ገዢው ፓርቲ ጥሩ ሲሰራ ጥሩ እየሰራ ነው ማለት አስፈላጊ ነው፡፡ ሊበላሽ ሲል ደግሞ ይሄ ትክክል አይደለም ማለት ወሳኝ ነው፡፡

ቀደም ሲል ከነበረው የተቃውሞ አሰራር (ማውገዝና መዛለፍ) አሁን ወዳለው ቀጥታ ሽግግር ማድረግ በጣም ከባድ ነበር፡፡ በእኛ እምነት የለውጥ ሂደት በጣም ፈታኝ የሆነ ጥንቃቄ የሚጠይቅ በእውነት መቆም የሚያስፈልገው ነው፡፡ እነዚህ አካሄዶቻችን አስተችተውናል፡፡ ከተነሱብን ትችቶች ለሀገር የሚጠቅመውን እናስቀጥላለን፡፡ መማር ባለብን እንማራለን፡፡ ለምሳሌ ያህል በአፋጣኝ መግለጫ መስጠት በሚቻልበት ጉዳዮች ላይ በአፋጣኝ መግለጫ መስጠት ይኖርብናል፡፡ በሁሉም ጉዳዮች ላይ የፓርቲውን አቋም ቶሎ አለማሳወቅ ላይ የሚታየውን ክፍተትም እናስተካክላለን፡፡ ይደር ይዋል የምንለው ጉዳይ ሳይኖር ቶሎ ቶሎ መግለፅ ያለብንን ጉዳይ በአፋጣኝ እንገልፃለን፡፡

መግለጫ አላወጣችሁም ወይም የሕዝቡን ጥያቄ ቸል ብላችኋል የሚል ጥያቄ አይደለም የሚነሳብን፡፡ ሲነሳብን የነበረው ጥያቄ እኛ በምንፈልገው ልክ ችግሩን አልገለፃችሁትም የሚል ነው፤ ብዬ ነው የማምነው፡፡ እኛ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ እኩል ነው የምንመለከተው፡፡ የእከሌ ብሔር፣ የእከሌ ሐይማኖት አንልም፡፡ አንድን ዘውግ አንስተን አለመተቸታችን ላያስደስት ይችላል፡፡ ይህን ደግሞ ወደፊትም አናደርገውም፡፡ መግለጫ ስናወጣም ከዚህ በፊት ባልተለመደ መልኩ መግለጫ ከማውጣታችን በፊት ጥያቄዎችን እንጠይቃለን፡፡ ባሉን መዋቅሮቻችን የማጣራት ሥራ እንሰራለን፣ የምንናገረው ነገር ሰላም ያመጣል? የሚለውን እንፈትሻለን፡፡ እኛ ብንሆን ኖሮ ምን ነበር የምናደርገው ብለን ራሳችንን እንጠይቃለን፡፡ መፍትሔ ማመላከት እንችላለን ወይስ ዝም ብለን መፍረድ ብቻ ነው የሚሆነው ድርሻችን የሚለውን እንፈትሻለን፡፡ ይሄ ከኖርንበት የተቃውሞ አሰራር (ዘሎ ማጋለጥና ማውገዝ) ወጣ ያለ ነው፡፡ ይህ ሽግግር ሊያስተች ይችላል፡፡ መታረም ያለበትን እናርማለን፡፡ የምናምንበትን እናስቀጥላለን፡፡

ከገዢው ፓርቲ ጋር ያለው ግንኙነት ለኢትዮጵያውያን ዜጎች ሁሉ በእኩልነት የቆመ ሀገርን የሚያስቀጥል የእውነት ዴሞክራሲያዊ ስርአትን የሚያመጣ አካሄድ እስካየን ድረስ ብቻ ነው የሚሆነው፡፡ ሽግግሩ በትክክል እስከቀጠለ ድረስ ብቻ ነው ከገዢው ፓርቲ ጋር ያለን ቃልኪዳን ሊቀጥል የሚችለው፡፡ ይህን ደግሞ የተስማማው ኢዜማ ብቻ አይደለም፡፡ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ቃልኪዳን ሰነድ ተፈራርመዋል፡፡ ምን ያህሉ ነው እየተገበረው ያለው? የሚለውን ሕዝብ በደንብ እየታዘበ ነው የሚል እምነት ነው ያለኝ፡፡ በእኛ በኩል ግን ለሕዝብ ብሶቶች የምናሰማው ጩኸት በቶሎና በተመጣጣኝ ማድረግ እንዳለብንና ከሕዝብ ጎን በፍጥነት መቆም እንዳለብን ያካሄድነው ግምገማ አመላክቶናል፡፡ ይህንን ክፍተታችንንም እናርማለን፡፡

*ይህ ትችት ሊቀርብ የቻለበት ምክንያት የኢዜማን መርሆች ካለመረዳት ሊሆን አይችልም? እርስዎ ይህንን አያምኑም? መርሆዎቹን ካለመረዳት የሚመነጭ ከሆነም አመራሩ መርሆቹን ለማስረዳት ምን ያህል ጥረት አድርጓል?*

እንዳልከው መርሆቹን ካለመረዳት ይመነጫል፡፡ ከልምዱም ቶሎ መላቀቅ አለመቻልም ነው፡፡ አንድ ኃላፊነት የሚሰማው የፖለቲካ ድርጅት እንዴት ነው መንቀሳቀስ ያለበት? ሀገር መተራመስ መፍረስ የለበትም፡፡ ባለው ላይ እየደመርንና እየጨመርን ነው መሄድ የሚገባን፡፡ ሁልጊዜ ከዜሮ መጀመር የለብንም ብሎ ከሚያምን የፖለቲካ ስብስብ ምንድነው የሚጠበቀው የሚለውን በማስረዳት አባሉ፣ ደጋፊው፣ ሕዝቡ ወደዚህ አስተሳሰብ እንዲመጣ ማድረግ ቀላል ሥራ አይደለም፡፡ ብዙ ጊዜን የሚጠይቅም ነው፡፡ ምንም ብትሰራ ከትችት ልትፀዳ አትችልም፡፡

ኢዜማ ያለውን ትልቅ መዋቅርና የሰው ሀይል በመጠቀም ወደ ብጥብጥና ሁከት ቢገባ ኖሮ ምን አይነት ችግር ሊፈጥር ይችል ነበር የሚለውን ማጤን ያስፈልጋል፡፡ በዝምታው ያዋጣውን ነገር ብንቆጥረው ለኢትዮጵያ በጣም ትልቅ አስተዋፅኦ ነው ያደረገው ብዬ ነው የማምነው፡፡ ለእያንዳንዱ ነገር መልስ አለመስጠት መጥፎ ጎኖች ቢኖሩትም ለሚከፈተው ፕሮፖጋንዳ ሌላ አፀፋ አለመስጠት የራሱ የሆነ ጉዳት አምጥቷል፡፡ ይህንን በመመከት ደረጃ የኢዜማ ሕዝብ ግንኙነት ምን ያህል ሄዷል የሚለውን ካየን በጣም ደካማ ነው፡፡ ፓርቲው ግልፅ የሆነ አላማ ባላቸው ዘውግ ድርጅቶችና ምን እናድርግ ▶



ብለን ስንጠይቃቸው መፍትሔ በሌላቸው ቡድኖች ሲቀጠቀጥ ነበር፡፡ ኢዜማ፣ ይህን ምን ያህል መክቷል የሚለውን በግምገማችን ወቅት እንዳነሳነው በጣም ደካማ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በፖሊሲ ዝግጅትና በራሳችን የውስጥ ሥራ ላይ ነበር ተጠምደን የነበረው፡፡ ዞሮ ዞሮ ግን እውነት ምንም ብትቀጥን አትበጠስም፡፡ እውነት እስካለህ ድረስ ምንም አይነት ቀለም ብትቀባም በላብህና በደምህ ልትጠርገው ትችላለህ፡፡

*የኢዜማ ማኅበራዊ መሰረት የትኛው የሀገሪቱ ክፍል ነው ትላላቹህ? ማኅበራዊ መሰረታችንን በመለየት በኩል በቂ ሥራ ሰርተናል ብላቹህ ታስባላችሁስ?*

ይህ ጥያቄ ብዙ ጊዜ የሚነሳ ነው፡፡ ለየትኛው መደብ ነው የቆምከው እንደማለት ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ከተማን መሰረት ያደረገ፣ ለታችኛው፣ ለላይኛው፣ መካከለኛ ገቢ ላለው ነው የቆምኩ ሲባል እንሰማለን፡፡ ይህ ለኢዜማ የሚሰራ አይመስለኝም፡፡ ኢዜማ፣ የዜጎች ፓርቲ ነው፡፡ ለዚህኛው መደብ ነው የቆምኩት የሚለው አመለካከት ባለፉት ዓመታት የሚሰራ ነበር፡፡ አሁን ግን የሚሰራ አይመስለኝም፡፡ ሁሉንም ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል ስርአት ነው የሚያስፈልገው፡፡ ለታችኛው ወይም ለድሃው የማኅበረሰብ ክፍል የሚፈጠረው የሥራ ዕድል ለላይኛው ጠቃሚው ነው፡፡ ያለዘላቂ ሰላምና ዴሞክራሲ ሊረጋገጥ አይችልም፡፡ እኛ የምንከተለው የማኅበራዊ ፍትሕ ፍልስፍና ለድሃው የቆመ ቢመስልም የድሃው ማግኘት ለሀብታሙ በሰላም ለመኖርም ሆነ በኢኮኖሚ ለማደግ ወሳኝ ነው፡፡ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍል በእኩልነት፣ በዘላቂ ሰላምና በዴሞክራሲ ሊያኖር የሚችል አርሶ አደሩን፣ ወጣቱን፣ የከተማ ነዋሪውን፣ አዛውንቱን... በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ የሽግግር ሂደት ሊጠቅም የሚችል የፖለቲካ ፍልስፍና ነው ያለን፡፡ በአጭሩ ለመግለፅ ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍል በሰላምና በጤና ሊያኖር የሚችል እሳቤ ነው ያለን፡፡

*2012 ዓ.ም ኢትዮጵያ በበርካታ ችግሮች ውስጥ አልፋለች፡፡ አንዳንድ ወገኖች እነዚህን ችግሮች በማስተዋል የሀገሪቷ ሽግግር አደጋ ላይ ወድቋል ይላሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ኢትዮጵያ ወደ አንድ ግለሰብ አምባገነን ሽግግር እያደረገች ነው ይላሉ፡፡ ኢዜማ በእዚህ ላይ ምን ይላል?*

የሽግግር ሂደቱን ባነሳኸው መልኩ የሚገመግሙት ኢትዮጵያውያን በጣም ብዙ ናቸው፡፡ በእኔም ዕይታ ከእውነቱ ብዙም የራቀ አይመስለኝም፡፡ እስከዛሬ ድረስ ሽግግር ተሳክቶልን አያውቅም፡፡ በዘመናዊት ኢትዮጵያ እንኳ በጣም ብዙ ጊዜ ተሞክሯል፡፡ በ1953፣ በ1967፣ በ1983 እንዲሁም በ1997 ዓ.ም ተሞክሮ አልተሳካም፡፡ በገዢው ፓርቲ በኩል ያሉ ሰዎች ሽግግሩን የረሱት ይመስለኛል፡፡ አነጋገራቸውም ሆነ አሰራራቸው ያንን ያመላክታል፡፡ አንድን ሥራ ለመሥራት ፕሮግራም ቀርፆ፣ ፖሊሲ አዘጋጅቶ፣ በፖሊሲ ተወዳድሮና ሕዝብን አሳምኖ ነው ሊሰራ የሚችለው፡፡ ዝም ብሎ በመነሳት ፕሮጀክቶች ተጀምረው ሊሰሩ አይገባም፡፡ ዋናውን የሽግግር ፕሮጀክት ረስተውታል ብለን ስለምናስብም ነው፤ በየመግለጫዎቻችን ይህንን ለማስታወስ ጥረት የምናደርገው፡፡

ኢዜማ፣ ከመመስረቱ በፊት ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድን (ዶ/ር) ዋሺንግተን ዲሲ በተካሄደ ስብሰባ ላይ አግኝቼያቸው ነበር፡፡ በዛን ወቅት እኛ (ሰማያዊ ፓርቲ) የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም ግፊት እያደረግን ነበር፡፡ በኦፌኮና በመድረክ አካባቢ ያሉ ሰዎች ደግሞ የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ይቋቋም ይሉ ነበር፡፡ ለለውጥ ሀይሉ በነበረው ድጋፍ የተነሳ ያንን ጥያቄ መግፋት አልተቻለም፡፡

ሽግግሩ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል? በሽግግር ወቅት ምን መሰራት አለበት? ምንስ መሰራት የለበትም? ሽግግር እንዴት ነው የሚገለፀው? ሽግግርን የሚቆጣጠር የሽግግር ምክር ቤት ይቋቋም ብዬ ጥያቄ አንስቼላቸው ነበር፡፡ ‹‹ግድ የለም፤ እኔ አሸጋግራችኋለው›› ብለው ነው ምላሽ የሰጡት፡፡ ኢዜማ ያሸጋግሩናል ብሏል ተብሎ ሲነሳ እንሰማለን፡፡ ይህንን በደንብ ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ‹‹ግድ የለም እኔ አሸጋግራችኋለው›› ያሉት ራሳቸው ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የቪዲዮ ክምችት ላይ ይህንኑ ማግኘት ይቻላል፡፡ ኢዜማም ያን ጊዜ አልተመሰረተም፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ትልቁ ፕሮጀክት የዴሞክራሲ መሰረት መጣል ነው፡፡ ይህንን ስል ሌሎች የሚሰሩ ነገሮች ለኢትዮጵያ አያስፈልጓትም እያልኩ አይደለም፡፡ መቅደም ያለበት የዴሞክራሲን መሰረት መጣል ነው፡፡ ለውጡ ተደናቅፏል፣ ተቀልብሷል፣ ተሰናክሏል... የሚል ተስፋ የቆረጠ እሳቤ የለንም፡፡ ለማስተካከል ዕድሉ አለ፡፡ ነገር ግን ቅን ልቦና ይፈልጋል፡፡ በተለይ በገዢው ፓርቲ በኩል ያሉ ሰዎችን ቅን ልቦና ይጠይቃል፡፡ እያንዳንዱ ፓርቲና ዜጋ ለኢትዮጵያ የሚመኘው ህልም እንዳለው ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ ይህ እንዲሰራ የሚፈቅደው ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ እያንዳንዱ የሚመሰቃቀሉ ነገሮች ነገ ሊረግቡ እንደሚችሉ ወቀሳም ሆነ ጭብጨባ ነገ ሊረሳ እንደሚችል ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህም ሂደቱ በጣም ችግር ውስጥ እንዳለ በደንብ እንረዳለን፤ ገምግመንዋልም፡፡ አብዛኛው ችግር የሚመጣው ግን ከገዢው ፓርቲ በኩል እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ጭልጥ ብሎ አክትሞለታል ከሚሉት ወገን አይደለንም፡፡ ቅን ልቦና ካለና ለሀገር ማሰብ ከተቻለ ችግሮቹን ማስተካከል እንችላለን፡፡ ለዚህ ደግሞ እንደ ሀገር የሰው ሀይልም ሆነ የሀሳብ እጥረት እንደሌለብን ይታወቃል፡፡ ያቃተን መደማመጥ ነው፡፡ ሁሉንም ያሳተፈ የእውነት የሆነ ውይይት ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ካደረግን ሽግግሩም ሆነ ኢትዮጵያ ተስፋ አላት የሚል እምነት ነው ያለኝ፡፡

*ሽግግሩ መስመሩን ስቷል በሚል ትችት የሚሰነዝሩ ወገኖች ገዢው ፓርቲ ቅን ልቦና ያለው አይመስልም ይላሉ፡፡ ቅን ልቦና እንደሌለው ማሳያ የሚሆነውም የምርጫ መቃረብን ተከትሎ ተቃናቃኞቹን ወደ ወሕኒ ወርውሯል ይላሉ፡፡ የዴሞክራሲ መሰረት ለመለካት እንደ መመዘኛ ከሚቀመጡ መስፈርቶች መሀልም የጠንካራ ተቋማት ግንባታ አንዱ ነው፡፡ ጠንካራ ተቋማት ለመገንባት የተደረገው ሙከራም ለሚዲያ ፍጆታ ከመዋል በዘለለ ጠንካራ ተቋማት ለመገንባት ጥረት ተደርጓል ብለው አያስቡም፡፡ ገዢው ፓርቲ አቅሙ ብቻ ሳይሆን ፍቃደኝነቱም ሆነ ዝግጁነቱም ነው የሌለው ይላሉ፡፡ እርስዎ በዚህ ላይ ምን ይላሉ?*

እዚህ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ እንደ ፈንጂ መርማሪ እያንዳንዱን እርምጃ በጥንቃቄ መራመድን ይጠይቃል፡፡ ችግሩን ለአንድ አካል ብቻ ካሸከምነው ከበፊቱ አልተማርንም ማለት ነው፡፡ ከዚህ በፊት የነበሩ የሽግግር ሂደቶች እንዴት ነው የነበሩት ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ አውሬ ሰዎች ይመጡብናል፡፡ አንዳንዴ ደግሞ እኛ አውሬ እናደርጋቸዋለን፡፡ ሁለቱም እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አሁን ላየናቸው ምስቅልቅሎችና ለደረሰው መደነቃቀፍ አንድ አካል ብቻ ነው ተጠያቂ ማለት በጣም ያስቸግራል፡፡ እዚህ ሀገር እንደኖረ ሰው ሌሎችም ተዋናይ እንደነበሩ ሁላችንም ምስክሮች ነን፡፡

የተዋረደ ሰው ይዞ የተከበረ ሀገር መመስረት አይቻልም፡፡ እንደ ሕዝብ ጥንቃቄ ማድረግና ሰውን የሚገባውን ክብር መስጠት በጣም አስፈላጊ ይመስለኛል፡፡ በመንግሥት ውስጥም ሆነ በተቃውሞ ጎራ ያሉትን ▶

ሰዎች ሰድቦና አዋርዶ የተከበረ ሀገር ባለቤት መሆን አይቻልም:: በስርአት መነጋገር አስፈላጊ ነው:: ዋናውና ትልቁ ጉዳይ ያለው ግን በገዢው ፓርቲና በጠቅላይ ሚኒስትሩ እጅ ነው:: ከባለፉት መማር ያስፈልጋል:: አፄ ኃይለ ስላሴ ከሰሩት ስህተት፣ ፕሬዝደንት መንግሥቱ ኃይለማሪያምና ሌሎች መሪዎች ከሰሩት ስህተት መማር ያስፈልጋል:: ትልቅ መሪ ማለት የነገውን ሰርቶ ማለፍ የሚችል መሪ ማለት ነው:: በኢትዮጵያ ሁኔታ ደግሞ ጠንካራ ሰዎች እንጂ ጠንካራ ተቋማት የሉንም:: መለስ ብለን ወደ ኋላ ስንመለከት ፕሬዝደንት መንግሥቱም ሆነ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሁሉንም ተቋማት የሚቆጣጠሩ መሪዎች ነው የነበሩት:: የአፄ ኃይለ ስላሴም ተመሳሳይ ነው የነበረው:: ከዚህ በመማር እንዴት ነው ስልጣንን ለሕዝብ የምሰጠው የሚለውን ማሰብ ያስፈልጋል:: ስልጣኑን ሕዝቡ መያዝ አለበት:: ሕዝብ በቀበሌና በወረዳ ደረጃ መምረጥ መቻል አለበት:: እነዛ የተመረጡት ሰዎች በዞን፣ በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ መሪ መሆን መቻል አለባቸው:: የሚመረጡትም በያዙት ሀሳብ መሆን መቻል አለበት:: ይህንን ለማድረግ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ቅንነት የሚጠይቅ ጊዜ ላይ እንዳለን ይገባኛል:: ሌላው በዛ ደረጃ ባይሆንም ከዛ ባልተናነሰ መልኩ ወሳኝ የሆነ ኃላፊነት አለበት:: ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት ሰፊውን ድርሻ የሚወስዱት ጠቅላይ ሚኒስትሩና ገዢው ፓርቲ ቢሆንም ሌሎች ትልቅ ሚና አላቸው:: እንደ ትውልድ የምንወቀስበት፣ ከተሳካ ደግሞ እንደ አድዋ ድል የምንመሰገንበት ነው የሚሆነው::

*ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ (ዶ/ር) ቀደም ብለው ካነሷቸው መሪዎች ምን ሊማሩ ይገባል ብለው ያስባሉ?*

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ በደንብ ማወቅ ያለባቸው ነገር ቢኖር ሌሎች ሰዎች ስህተት የሰሩት ኢትዮጵያን ስለሚጠሉ አይደለም:: ለኢትዮጵያ ያሏት እነሱ ብቻ ስለሚመስላቸው ነው:: እነሱ ሲሄዱ የኢትዮጵያ ፀሃይ አብሮ የሚጠፋ ስለሚመስላቸው ነው:: ይህ ደግሞ እንደማይሆን ቢያንስ እሳቸው ምስክር ናቸው:: አቶ መለስ ዜናዊ የሞቱ ጊዜ ካድሬዎቻቸው ፀሀይ የጠለቀች ነበር ያስመሰሉት:: ይህ ግን አይደለም የሆነው:: ኢትዮጵያ በጣም ትልቅ ሀገር ናት:: ሰዎች አሏት:: ያቃታት ስርአት መዘርጋት ነው:: ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት ሕዝብ የሚፈልገውን የሚመርጥበትን፣ ያልፈለገውን የሚያነሳበትን ሕዝብ እውነተኛ አለቃ ሆኖ የሚያልፍበትን ስርአት ዘርግቶ ማለፍ ነው ዋና ተግባር ሊሆን የሚገባው::

«ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከእኛ በተጨማሪ ከደቡብ አፍሪካ የቀድሞ መሪ ኔልሰን ማንዴላም መማር የሚችሉ ይመስለኛል:: ማንዴላ፣ ብዙ ዓመት ትግል አድርገው 4 ዓመታትን ብቻ ነው በስልጣን ላይ የቆዩት:: ለደቡብ አፍረካውያን ግን የዘላላም ፕሬዝዳንት ናቸው:: በመቆየት አይደለም ታሪክ የሚሰራው:: በ15 ቀናትም ሆነ በ2 ዓመታት ብዙ ታሪክ ይሰራል::»

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከእኛ በተጨማሪ ከደቡብ አፍሪካ የቀድሞ መሪ ኔልሰን ማንዴላም መማር የሚችሉ ይመስለኛል:: ማንዴላ፣ ብዙ ዓመት ትግል አድርገው 4 ዓመታትን ብቻ ነው በስልጣን ላይ የቆዩት:: ለደቡብ አፍረካውያን ግን የዘላላም ፕሬዝዳንት ናቸው:: በመቆየት አይደለም ታሪክ የሚሰራው:: በ15 ቀናትም ሆነ በ2 ዓመታት ብዙ ታሪክ ይሰራል:: ያልተሰራበት ሀገር ነው ያለን:: ዋናው ያቃተን ነገር ስልጣንን ለሕዝብ ማሸጋገር ነው:: እዚህ ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል:: ሌላው ነገር አያስፈልግም ሳይሆን ሌሎች ይሰሩታል ከሚል እሳቤ ነው:: ለምሳሌ አረንጓዴ ልማት የራሱ የሆነ ሴክተር መስሪያ ቤት አለው:: የሕዳሴ ግድብም የራሱ የሆነ መሪ አለው:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ እኔ አሸጋግራችኋለው እስካሉ ድረስ ትኩረት ሊሰጡ የሚገባው ሽግግሩ ላይ ነው:: እስካሁን ድረስ በአገዛዝ ውስጥ ነው ያለነው:: ሕዝብ የመረጠው መንግሥት አይደለም በስልጣን ላይ የሚገኘው:: የምንሻገረው ላያችን ላይ መጥቶ ከተቀመጠ መንግሥት፣ ሕዝብ ወደ መረጠው መንግሥት ነው:: ዋናው ፕሮጀክት ሊሆን የሚገባውም ወደዛ የምንሸጋርበትን ስርአት ማበጀት ነው ብዬ ነው የማስበው:: ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሌት ተቀን ማሰብ ያለባቸው ይህንኑን ነው:: ከሌላው ተምረዋል የምንለውም ይህን ያደረጉ እንደሆነ ነው::

*ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አሕመድ በያዝነው የ2013 ዓ.ም ምርጫ እንደሚካሄድ ገልፀዋል:: ለፓርቲያቸው ብልፅግና የሚያሰጋ የፖለቲካ ፓርቲ የለምም ብለዋል:: ይህንን ንግግራቸውን እንዴት ተመለከቱት? ኢዜማስ ለብልፅግና ፓርቲ ተገዳዳሪ ሆኖ መቅረብ ይችላል?*

የፖለቲካ ፓርቲ ሲጠራ ብልፅግና ፓርቲ የሚጠራ አይመስለኝም:: መጀመሪያ የሚጠራው ኢዜማ ነው:: ከዚህ በኋላ ገዢው ፓርቲ ወይም ብልፅግና የሚባለው ፓርቲ ቢጠፋ ወይም ሀገር ማስተዳደር ቢያቅተው ሀገር ይፈርሳል የሚል እሳቤ ሕዝብ ውስጥ የለም:: ብልፅግና ባይችል ኢዜማ አለ የሚል ሀሳብ ይነሳል:: ገዢው ፓርቲ የለምና ሀገር ችግር ውስጥ ይገባል የሚል እሳቤ ሕዝብ ዘንድ ያለ አይመስለኝም:: ይህንን ማድረግ በመቻላችንም ትልቅ የቤት ሥራ ሰርተናል ብዬ ነው የማምነው:: ኢዜማውያን ለሀገራቸው ትልቅ ሥራ ሰራን ካሉም ይህኛው ትልቁ አስተዋፅአዋቸው ይመስለኛል::

የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሙሉ ቃለምልልስ አዳምጨዋለሁ:: ጥሩ ገለፃዎች አሉት:: የተጠየቁትን ጥያቄ ግን አልመሰሉም:: እሸነፋለሁ ብለው ይሰጋሉ ወይ? የሚል ጥያቄ ነው ተነስቶላቸው የነበረው:: ጥያቄውን መልሰውታል ብዬ አላምንም:: ጥያቄውን ዞሩት እንጂ አልመለሱትም::

ተወዳዳሪ ሀሳብ ያለው ፓርቲ የለም ያሉት ፍፁም ስህተት ነው:: ስልጣን ላይ በወጡበት ጊዜ ፓርቲዎች ማለት ሌላ ተፎካካሪ ሀሳብ ያላቸው ወንድሞች ናቸው ነበር ያሉት:: ይህንን በሁለት ዓመት ውስጥ ከረሱት በጣም ይገርማል:: ስለዚህም ይህ ንግግራቸው ትክክል አይደለም:: በእኛ በኩል እሳቸውን የምንመለከተው ሊጠቅም የሚችል ሀሳብ ይዘው የመጡ ወንድም ናቸው ብለን ነው:: እኛንም እንደዛ ይመለከቱናል ብለን ነበር የምናስበው:: በጠቅላይ ሚኒስትር ፅ/ቤት፣ በምርጫ ቦርድና ኢትዮጵያን በሚወዱ የተለያዩ ድርጅቶች በሚያካሄዱት ስብሰባዎች እሳቸውን ጨምሮ የሚጠሩን ሀሳብ አላቸው ብለው ነው:: ሀሳብ አላቸው ብለው የሚጠሯቸውን ወንድምና እህቶቻቸውን ሀሳብ የላቸውም ማለታቸው በደንብ አስበውበት የተናገሩት አይመስለኝም::

በፓርቲ ደረጃ ከተመለከትንም ኢዜማ፣ ብልፅግናን ቢያንስ በ 6 ወራት ይበልጠዋል:: በወርሃ ግንቦት 2011 ዓ.ም



«ሳንቲምን ወደ አይንህ ባስጠጋህት ቁጥር ዓለምን ትጋርድህለች ይላሉ:: ካራቃት ምንም ነገር አትከልልህም:: ካስጠጋህት ግን መጀመሪያ ሕንፃውን ከዛ ከተማውን ትጋርድሃለች:: በደንብ ካስጠጋህት ደግሞ ዓለምን ትጋርድሃለች:: ስልጣንም ልክ እንደዛ ነው:: »

ነው 10 የፖለቲካ ድርጅቶችን አንድ ላይ አድርገን የተመሰረትነው:: ሕዳር 2012 አካባቢ ነው በውህደት ብልፅግናን መሰረትን ያሉት:: በሀሳብ ደረጃም ብዙ ሀሳቦችን ከኢዜማ ወስደዋል:: ማኅበራዊ ፍትሕንም ሆነ ወደ ታች የወረዳ አደረጃጀትን ከእኛ ወስደዋል:: ሀሳብ ያለው ድርጅት ስላለ ነው ሀሳብ የሚወስዱት:: ይህንንም እሳቸውም በደንብ ያውቃሉ:: ሀሳብ ያለው ድርጅት የለውም ያሉት አባባላቸው ስህተት ነው:: መታረምም አለበት:: ሀሳብ ከሌለ በምንድነው የምንወዳደረው?! እዚህ ሀገር የፖሊሲ ሰነድን የማዘጋጀትን ሂደት በሚመለከት ቀደም ሲል ቅንጅት አሁን ደግሞ ኢዜማ ነው ያካሄደው:: በመግለጫ የሚወጣ ሀሳብ ብቻ ሳይሆን በፖሊሲ ደረጃ የተሰነደ ገዢው ፓርቲን ጨምሮ ሌሎችም ፓርቲዎች ያልዳሰሷቸውን ርዕሰ ጉዳዮች የሚዳስሱ የፖሊሲ አማራጮች ያለን ድርጅት ነን:: ንግግራቸው ለኢዜማ የሚመጥን አይደለም:: ለእሳቸውም ይመጥናል ብዬም አላስብም:: ትክክለኛ አገላለፅም አይደለም::

ብልፅግና የተባለው ድርጅት በሚመለከት በእርግጠኝነት መናገር የምችለው በጥቅም የተሳሰሩ ሌቦች ያሉበት ዋሻ መሆኑን ነው:: ይህንን ደግሞ በሚያደርጓቸው ተግባሮቻቸውና ዜጎች ላይ በሚያደርሷቸውን ነገሮች በመመልከት መረዳት ይቻላል:: ሽግግሩን የረሱ በሚመስሉ መልኩ የሚሄዱባቸው መንገዶችም በአጠቃላይ ብልፅግና የሚባለው ፓርቲ ገና ያልጠራ እንደሆነ ያሳያል::

ዊንስትን ቸርችል፣ በጣም ጥሩ የሰሩና እንግሊዝ ሁለተኛ የዓለም ጦርነትን እንድታሸንፍ ያደረጉ ነገር ግን ያልተመረጡ ሰው ናቸው:: ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ ጥሩ ሰርተናል ብለው ቢያስቡ እንኳ ዜጋው በመሰልቸትም ላይመርጣቸው እንደሚችል መረዳት መቻል አለባቸው:: ሕዝብ አዲስ ፊት ማየት ሊፈልግ ይችላል:: እንደ ፓርቲ አዳዲስ ፊትና አዳዲስ ሀሳብ ማምጣት መቻል አለባቸው:: ከነበረባቸው የዘውግ መዋጮ ወደ ችሎታ ከፍ ማለት መቻል አለባቸው:: ኢትዮጵያን የሚያዩበትን ዕይታ በደንብ መቀየር አለባቸው:: በአዲስ አበባና በኢትዮጵያ ያላቸውን ምልከታ ማረም መቻል አለባቸው:: የአንድ ሳምንት የአክቲቪስት ጩኸት ምንም አይጠቅማቸውም:: ሀሳባቸውን አጥርተው ነው መወዳደር የሚገባቸው:: ካለ እኛ ውጪ ሀሳብ ያለው የለም የሚሉ በተቃውሞ ጎራ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ነበሩ:: አሁን ላይ ግን እንዲያ ሲሉ የነበሩት ፓርቲዎች ራሳቸው የሉም:: በመንግሥትም በኩል አቶ መለስ ተመሳሳይ ነገር ይናገሩ ነበር::

የኢትዮጵያ ሕዝብም በጣም ከባድ ሕዝብ ነው:: የአዲስ አበባ ሕዝብ መርማሪ ሕዝብ ነው:: እያንዳንዱ የምንናገረውንና የምናስበውን ነገር በየጊዜው እየመዘገበ የሚይዝ ነው:: በአንድ ቀን ግርግርና በአንድ ሳምንት የካድሬ ጫጫታ ብቻ የሚመርጥ ሕዝብ አይደለም:: ስለዚህ ሌላ ሀሳብ ያለው የፖለቲካ ስብስብ የለም ብሎ መናገር በኋላ መደናገጥን እንዳያመጣ መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: ሚያዚያ 29 ቀን 1997 ዓ.ም አቶ መለስ ዜናዊ ለፓርቲያቸው የተጠራውን የድጋፍ ሰልፍ አይተው ምንም ሳናጭበረብር ምርጫ እናሸንፋለን ብለው ተናግረው ነበር:: በማግስቱ ለቅንጅት ድጋፍ በተጠራው የሚያዚያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም ሰልፍ ላይ የሕዝቡን ምላሽ አይተውታል:: የምርጫው ጊዜ ደርሶ ስለነበርም የማስተካከያ ጊዜም አላገኙም:: ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ ግን ለማስተካከል ጊዜ አላቸው:: የተናገሩት ነገር ፍፁም ትክክል አይደለም:: ሀሳብ ያላቸው ፓርቲዎች አሉ:: በእኛ ግምገማ እንደውም 50 ሲደመር 1 ድምፅ ማግኘት ለሁሉም ፓርቲ በጣም ከባድ ነው የሚሆነው:: ተባብሮ መንግሥት የመመስረቱ ነገር ግዴታ ሊሆን ይችላል:: አራትና አምስት ትላልቅ የፖለቲካ ጎራዎች አሸናፊ ሊሆኑ ይችላሉ:: ያንን ለመካፈል በደንብ መሥራትና ልቦናን ማዘጋጀት ያስፈልጋል:: ተጣምሮ መንግሥት ለመመስረትም መዘጋጀት ያስፈልጋል:: 99 በመቶ አሸነፍኩ ምናምን ማለት ራሳቸው እንዳሉት የጨረቃ ምርጫ ነው የሚሆነው::

ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ወንድማዊ ምክር አለኝ:: ምርጫ ባይወዳደሩ ነው የሚሻላቸው የሚል ፅኑ እምነት ነው ያለኝ:: እኔ አሸጋግራችኋለሁ አይደል ያሉት ስለዚህ በማሸጋገር ታሪክ የሚሰሩ፣ ድልድይ የሚሆኑ ሰው ብቻ እንዲሆኑ ነው እኔ የምመክራቸው:: ኃይሉ አርአያ (ዶ/ር) አንድ አባባል አላቸው:: ሳንቲምን ወደ አይንህ ባስጠጋህት ቁጥር ዓለምን ትጋርድህለች ይላሉ:: ካራቃት ምንም ነገር አትከልልህም:: ካስጠጋህት ግን መጀመሪያ ሕንፃውን ከዛ ከተማውን ትጋርድሃለች:: በደንብ ካስጠጋህት ደግሞ ዓለምን ትጋርድሃለች:: ስልጣንም ልክ እንደዛ ነው::

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፓርቲዬ ሊያሸንፍ ይችላል ወይስ አይችልም የሚል ነገር ውስጥ ከገቡ ሽግግሩን ሊመሩት አይችሉም:: ሁሉን ነገር ከተዉት ግን ሽግግሩ የት እንደቆመ የት እንዳለ የት እንደሚሄድ ከእነማን ጋር ሽግግሩን መምራት እንዳለባቸው ያውቃሉ:: እዚህ ውድድር ውስጥ ባይገቡም ነው የሚሻላቸው:: ጥያቄውን ያነሳላቸው ጋዜጠኛ ደካማ በመሆኑ ነው እንጂ ሽግግሩ ምን አይነት ፈተና እንደተጋረጠበት በደንብ እንዲታይዎት ቢተዉትስ ብሎ ጥያቄ ማንሳት የነበረበት:: ሀሳብ ያለው የፖለቲካ ፓርቲ የለም ላሉትም እንደ ኢዜማ፣ አብን፣ ኦነግ፣ ሕወሓት ያሉ ፓርቲዎች አሎ ብሎ መጠየቅ ነበረበት:: እሱም ጥያቄውን አላነሳም:: እሳቸውም መልሳቸው ፈር ያለው አይደለም::

አሸንፋለው ወይም አላሸንፍም የሚለው አይደለም ሊያሳስባቸው የሚገባው:: ሁሉን ነገር ትተው ሽግግሩን ብቻ በትክክል መምራት ነው የሚገባቸው:: ኃላፊነታቸውን ሊወጡ የሚችሉት ራሳቸውንም ሆነ ለሽግግሩ ያግዛሉ ብለው የሚያስቧቸውን ወንድምና እህቶች በሙሉ ከምርጫው ነፃ በማድረግ ነው የሚመስለኝ::

*ለነበረን ቆይታ በአንባቢዎቻችን ስም በጣም አመሰግናለሁ::*

እኔም አመሰግናለሁ!

# ‹‹ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሀሳብ ያለው ድርጅት የለም ማለታቸው ስህተት ነው። ይህ ንግግራቸው መታረምም አለበት።›› የሺዋስ አሰፋ

መስከረም6 ቀን 2013ዓ.ም (የዜናች መድረክ)



የኢዜማ ሊቀመንበር ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ ተወዳዳሪ ሀሳብ ያለው ፓርቲ የለም ያሉት ፍፁም ስህተት ነው ሲሉ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኀበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

በፓርቲያቸው የእስካሁኑ እንቅስቃሴና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ከዜጎች መድረክ ጋር ቆይታ ያደረጉት የኢዜማ ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን ላይ በወጡበት ጊዜ ‹‹ፓርቲዎች ማለት ሌላ ተፎካካሪ ሀሳብ ያላቸው ወንድሞች ናቸው›› ነበር ያሉት ሲሉ አስታውሰዋል ፡፡ የአሁኑ ንግግራቸውም ያኔ ካደረጉት ጋር እንደሚጋጭ ጠቁመዋል፡፡ በጠቅላይ ሚኒስትር ፅ/ቤት፣ በምርጫ ቦርድና ኢትዮጵያን በሚወዱ የተለያዩ ድርጅቶች በሚያካሄዱት ስብሰባዎች ላይ ኢዜማ እንዲካፈል የሚደረገውም ሀሳብ አለው ተብሎ ስለሚታመን እንደሆነ ገልፀዋል ፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትር ፅ/ቤት በሚያካሄደው ውይይትም ኢዜማ እንደሚካፈል ያስታወሱት ሊቀመንበሩ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሀሳብ አላቸው ብለው የሚጠሯቸውን ወንድምና እህቶቻቸውን ሀሳብ የላቸውም ማለታቸው በደንብ አስበውበት የተናገሩት አይመስለኝም ብለዋል፡፡

በፓርቲ ደረጃ ፓርቲያቸው ኢዜማ፣ ብልፅግናን ቢያንስ በ 6 ወራት እንደሚበልጠውና በግንቦት 2011 ዓ.ም ኢዜማ፣ 7 የፖለቲካ ድርጅቶችን አንድ ላይ በማክሰም እንደመሰረቱትና ከመሰረቱት በኋላም 3 የፖለቲካ ፓርቲዎች ከስመው እንደተቀላቀሏቸው በድምሩ 10 የፖለቲካ ፓርቲዎች ከስመው ኢዜማ ሊፈጠር እንደቻለ አስረድተዋል፡፡ በአንፃሩ ብልፅግና ሕዳር 2012 ዓ.ም አካባቢ ነው በውህደት የተመሰረተው ብለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሀሳብ ያለው ድርጅት የለም ማለታቸው ስህተት ነው፡፡ ይህ ንግግራቸው መታረምም አለበት ያሉት የኢዜማ ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋ፣ ሀሳብ ከሌለ በምንድነው የምንወዳደረው? ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ የፖሊሲ ሰነድን የማዘጋጀት ሂደት በሚመለከት ከቅንጅት ቀጥሎ በአግባቡ ማሰናዳት የቻለው ፓርቲያቸው ኢዜማ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በመግለጫ የሚወጣ ሀሳብ ብቻ ሳይሆን በፖሊሲ ደረጃ የተሰነደ ገዢው ፓርቲን ጨምሮ ሌሎችም ፓርቲዎች ያልዳሰሷቸውን ርዕሰ ጉዳዮች የሚዳስሱ የፖሊሲ አማራጮች አሉንም ብለዋል፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግርም ይህንን ታሳቢ ያላደረገና ለሚገኙበትም ቦታ የሚመጥን እንዳልሆነ ሊቀመንበሩ በአፅንኦት ተናግረዋል ፡፡ ትክክለኛ አገላለፅ ስላልሆነ ሊታረም ይገባዋል ብለዋል፡፡

▶





# ‹‹እምነታችንን በአንድ ሰው ላይ ካደረግን የበለጠ ችግር ውስጥ እንገባለን። እምነታችንን ተቋማት ላይ እናድርገው።››

## ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)የኢዜማ መሪ

መስከረም6 ቀን 2013ዓ.ም (የዜናች መድረክ)



ኢትዮጵያ ወደ ዴሞክራሲ የምታደርገው ሽግግር ያለ ጠንካራ ተቋማት ግንባታ ሊሳካ የሚችልበት እድል እንደሌለ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኀበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) መሪ ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) ተናገሩ፡፡

መሪው የጠንካራ ተቋማት ሚና ወደ ዴሞክራሲ ሊደረግ የሚገባውን ሽግግር በማገዝ ረገድ ትልቅ ሚና እንደሚጫወቱ ተናግረዋል፡፡ ብርሀኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) ከኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) ጋር በቅርቡ ባደረጉት ቆይታ ተቋማት በደንብ ተገንብተው እስካላቋ ድረስ አምባገነንነት ሊመጣ የሚችልበት እድል ሁሌም አለ ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ መንግሥት ጉልበቱን ተጠቅሞ በስልጣን ላይ እቀጥላለሁ ሲል አይሆንም የሚል የመከላከያ ሀይል፣ ፌደራል ፖሊስና ፍ/ቤት እስከሌለ ድረስ አምባገነንነት ሁሌም ሊኖር የሚችል ነው ብለዋል፡፡ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ማንበር ቀላል እንዳልሆነ የሚያስረዱት መሪው፣ በአንድ ሰው ላይ እምነት ከመጣል ይልቅ ተቋማትን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል ፡፡ ‹‹እምነታችንን በአንድ ሰው ላይ ካደረግን የበለጠ ችግር ውስጥ እንገባለን፡፡ ለዚህም ነው እምነታችንን ተቋማት ላይ እናድርገው የምንለው›› በማለት እምነት መጣል የሚገባው ተቋማት ላይ እንደሆነ እንጂ ግለሰብ ላይ ሊሆን እንደማይገባ ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ አጥብቆ ሰላምን እንደሚፈልግ ያነሱት የኢዜማ መሪ፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እምነት መጣል እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡ በሰላምና በጋራ ከመኖር ውጪ ሊመጣ የሚችለውን አደጋ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሶሪያ፣ ከሶማሊያ አይደለም የሚማረው ያሉት መሪው፣ ሕዝብ ከራሱ ታሪክ አይቶ ነው የሚማረው ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ ሀገር እንዴት ትርምስ ውስጥ ሊገባ እንደሚችል የኢትዮጵያ ሕዝብ አይቶታል ብዬ ነው የማምነው ያሉት ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ቢደረግ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት የሚያፋልሱ ሀይሎች የበላይነት የሚይዙበት ሁኔታ አለ ብዬ አላምንም ብለዋል፡፡ አምባገነንነት ሀገርን አረጋግቶ ለረጅም ጊዜ ያቆያል ብዬ አላምንም ያሉት መሪው ከዴሞክራሲ ውጪ አማራጭ እንደሌለ አብራርተዋል፡፡

መሪው፣ ወደ ዴሞክራሲና ወደ ሀገር አንድነት የሚወስደው ሂደት የተደቀነበት ስጋት በሚመለከት ባሳለፍነው ወር በበይነ መረብ በኩል በሀገር ውስጥና በውጪ ከሚኖሩ የኢዜማ ደጋፊዎች ጋር ባደረጉት ውይይት የተለያዩ ነጥቦችን ማንሳታቸው ይታወቃል፡፡ ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታ በቅጡ አለመረዳት፣ ኃላፊነት የማይሰማቸው የሚድያ አካላት እያሳደሩት ያለ ጫና፣ የተረጋጉ ተቋማት አለመኖር፣ በቀላሉ በስሜት የሚነዱ ሥራ አጥ የሆኑና ብዙ ድሆች ያሉበት ሀገር ባለቤት መሆን፣ በማኀበረሰቡ ዉስጥ የተፈጠረው የሞራል ዝቅጠት፣ በሁሉም ዘርፎች ላይ የሚታየው የብቃት ማነስ ወይም የአቅም ችግር፣ በቂ ዝግጅትና ችሎታ ያላቸው ሰዎች በመንግሥት ተቋማት ውስጥ አለመኖር፣ ፌደራሊዝሙ በዘር ላይ የተመሰረተ መሆኑና ይህንን ተከትሎ ሁሉን ነገር የሚሰሩ ሰዎች በዘር ከረጢት ውስጥ መደበቅ መቻላቸው እንደ ስጋት ካነሷቸው ነጥቦች መሀል ይገኙበታል፡፡ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንፍጠር ከተባለ ብቃት ያላቸው ሰዎች ከመንግሥትም ሆነ ከሌሎች ተቋሞች ወደፊት ማምጣት እንደሚያስፈልግ የሚናገሩት የኢዜማ መሪ ብርሀኑ ነጋ፣ ብቃት ያላቸው ሰዎች ወደፊት ማምጣት ካልተቻለ ዴሞክራሲያዊ ስርአት መገንባት አስቸጋሪ ነው የሚሆነው ብለዋል ፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ከማኀበረሰቡ ጋር ስር የሰደደ ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡ ስልጣን ላይ ያለ የፖለቲካ ሀይልን ሊገዳደሩ የሚችሉ፣ በምክንያት ሊሄዱ የሚችሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ማዳበርን እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል፡፡ ያለ ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዴሞክራሲያዊ ስርአት መገንባት እንደማይቻልም አስረድተዋል፡፡

ብርሃኑ ነጋ፣ ያነሱትን ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲ መፍጠርን በሚመለከት ፓርቲያቸው የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኀበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በስትራቴጂክ ግቡ ካስቀመጣቸው ግቦች መሀል አንደኛው ሲሆን፤ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት ለመፍጠር ብሎ 7 የፖለቲካ ፓርቲዎችን በማክሰም አንድ ሀገራዊ ፓርቲ መመስረት ችሏል፡፡ በእስካሁኑ ሂደቱም በ10ሩም ክልሎችና በሁለቱ የከተማ መስተዳድሮች 435 የምርጫ ወረዳዎች ላይ መዋቅሩን ዘርግቷል፡፡ ምሁራንን በማሳተፍም 45 የፖሊሲ ሰነዶችን መቅረፅ ችሏል፡፡

# ኢዜማ በኤካ ኮተቤ ጄኔራል ሆስፒታል በመገኘት ለታካሚዎች ድጋፍ አደረገ

## “ከኢዜማ ውጭ በዚህ ደረጃ ወደዚህ ቦታ መጥቶ የጎበኘ የፖለቲካ ፓርቲ የለም”

ዶ/ር ያሬድ አግደው

መስከረም6 ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የምርጫ ወረዳ 28 አመራሮችና አባላት በኤካ ኮተቤ ጄኔራል ሆስፒታል በመገኘት በኮሮና ቫይረስ ተይዘው በማገገሚያ ለሚገኙወገኖች በዓሉን በማስመልከት የኢዜማ ም/መሪ አንዱዓለም አራጌ፣ የኢዜማ ሊቀ መንበር የሺዋስ አሰፋ እና ሌሎች አመራሮች በተገኙበት በሆስፒታሉ ለሚገኙ የህክምና ድጋፍ እየተደረገላቸው ለሚገኙ ወገኖችእንኳን አደረሳችሁ በማለት በኢዜማ ምርጫ ወረዳ 28 አመራርና አባላት የተዘጋጀውን የበግና የወተት ድጋፍ ለሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ አስረክበዋል፡፡

ኢዜማ በህክምና ድጋፍ ላይ ላሉ ወገኖች የሰጠውን ስጦታ የኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል ዋና ሥራ አስኪያጅ ዶ/ር ያሬድ አግደው ከተረከቡ በኃላ “የኢዜማ አመራሮች መጥታችሁ ስላያችሁን፣ ስለጎበኛችሁን እናመሰግናለን፡፡ በዚህ ደረጃ ወደዚህ ቦታ ከኢዜማ ውጭ መጥቶ የጎበኘ የፖለቲካ ፓርቲ የለም፡፡ ኢዜማ ላደረገልን የሞራል ድጋፍና ስጦታዎች ሁሉ ሆስፒታሉንና ሰራተኞችን ወክዬ ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡ ”በማለት ኢዜማ ሆስፒታሉን በመጎብኘት፣ ድጋፍ ያደረገ የመጀመሪያው ፓርቲ መሆኑን በመግለጽ ምስጋናቸውን ቸረዋል፡፡

አዲስ አመትን በማስመልከት ብዙ መሰባሰቦች ስለሚኖሩ ሀኪሞች እና የጤና ባለሙያዎች የሚሰጡትን መመሪያ ኅብረተሰቡ በመከተል ራሱን ከወረርሽኙ መጠበቅ እንዳለበት አሁን ያለው ጊዜ በጣም ፈታኝ ወቅት በመሆኑ አንድ ላይ ተያይዞ ካልሆነ የማይታለፍ መሆኑን ለታዳሚዎቹ ገልጸዋል፡፡ በዓሉን አስመልክተውም አዲስ አመት እቅድ የምናወጣበት ጊዜ እንደመሆኑ መጠን በዚህ ሰዓት ማሰብ ያለብን ነገር በህይወት ለመቆየት ስንል ይሄን ጊዜ በጥንቃቄ ማለፍ እንደሚገባን፣ ለሌሎች ሞት ምክንያት እንዳንሆን አስፈላጊ ጥንቃቄዎችን ማድረግ አለብን በማለት መልእክት አስተላልፈዋል፡፡





# “ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎችን ከተጨማሪ አደጋ ለመከላከል ከፍተኛ ርብርብ ማድረግ ያስፈልጋል” ኢዜማ

መስከረም6 ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በሰው ሰራሽ እና በተፈጥሮ አደጋ የሚደርሱ ጉዳቶችን በሚመለከት መንግሥት አስቀድሞ መከላከሉ ላይ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ እንደሚገባ አሳሰበ።

ኢዜማ ዛሬ መስከረም 6 ቀን 2012 ዓ.ም “በሰው ሰራሽ እና በተፈጥሮ አደጋ ተጎጂ ዜጎችን መልሶ የማቋቋም ሥራ ተገቢው ትኩረት ይሰጠው!” በሚል ርዕስ ባወጣው መግለጫ በሰው ሰራሽ እና በተፈጥሮ አደጋ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመከላከል፣ የአደጋዎቹን ጉዳት ለመቀነስና ጉዳቱ ከደረሰ በኃላ ተጎጂዎችን ለማቋቋም በመንግሥት የሚወሰደው እርምጃ ያልተቀናጀ እና ደካማ ሆኖ አግኝቼዋለሁ ብሏል። ፓርቲው ያልተቀናጀ እና ደካማ ባለው የመንግሥት እርምጃ ሳቢያም የዜጎችን ሰቆቃ እየረዘመ ነው ሲል መንግሥትን ወቅሷል።

ጉዳዩ የሚመለከተው ብሔራዊ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ነው ያለው ኢዜማ፣ በየክልሉ የሚገኙ ቅርንጫፎች እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የክልል አመራሮች እና የፌደራል መንግሥት አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጡ ለወደፊትም ቀድሞ መከላከል ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ አሳስቧል። ከዓለም አቀፉ የኮሮና ቫይረስ ወረረሺኝ፣ የወባ ትንኝ መራባት እና የውሃ ወለድ በሽታዎች መዛመድን ከግምት በማስገባት ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎችን ከተጨማሪ አደጋ ለመከላከል ከፍተኛ ርብርብ ማድረግ ያስፈልጋል ብሏል ፓርቲው በመግለጫው።። የክረምቱ ዝናብ አሁንም ጠንክሮ በመቀጠሉ በጎርፉ ሳቢያ ከ2 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ላይ መጠኑ የተለያየ ጉዳት፣ እንዲሁም ከ400 ሺ ሰዎች በላይ ሊያፈናቅል እንደሚችል ግምት አለ ያለው ኢዜማ፣ ይህንን ግምት ተከትሎም መንግሥት አደጋ ይደርስባቸዋል ተብለው በሚታሰቡ አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎች ጋር አስቀድሞ በመነጋገር ሕዝቡ ችግር ውስጥ ከመግባቱ በፊት የመፍትሔ አቅጣጫ በማስቀመጥ አደጋውን ማስቀረት አለበት ብሏል።

ኢዜማ በመግለጫው እንዳመላከተው በእስካሁኑ የጎርፍ አደጋ በአፋር ክልል፣ በዱፍቲ፣ አሳይታ፣ አሚባራ፣ ግሎ፣ አፋምቦ እና ገዋኔ ወረዶች ቁጥራቸዉ ከ67,000 በላይ በሆኑ ሰዎች የጎርፍ አደጋ ጉዳት ሲደርስባቸው፣ ከ40 ሺ በላይ የሆኑት ተፈናቅለዋል ብሏል። 32,000 ዜጎች ደግሞ አደጋ ውስጥ እንደሚገኙ ጠቁሟል።

በኦሮሚያ ክልል በአዋሽ ተፋሰስ ተከትሎ ባሉ ወረዶች እና ከተሞች በተለይም ወንጂ፣ ፈንታለ እና የተወሰኑ የአዳማ ከተማ ሰፈሮች ላይ ከባድ ጉዳት ደርሷል ያለው ኢዜማ፣ በምሥራቅ ሸዋ ፈንታሌ ወረዳ ከ25,000 በላይ ሰዎች በጎርፍ አደጋ ሳቢያ ከመኖሪያቸው መፈናቀላቸውን ገልጿል። በአዳማ/ሶደሬ ከ700 በላይ አባወራ በጎርፍ ምክንያት ሲፈናቀል በንብረት ላይም ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን የጠቀሰው ኢዜማ፣ በወንጂ አካባቢም ከ10,000 ሰው በላይ በጎርፍ ምክንያት ከመኖሪያው መፈናቀላቸውን ጠቁሟል። ከአዋሽ ወንዝ ሙላት ጋር በተገናኘም ከ14 ሺ ሄክታር በላይ መሬት ላይ ያለ ሰብልና የመሠረተ ልማቶች ላይ ከባድ ጉዳት መድረሱን ፓርቲው በመግለጫው ጠቅሷል።

በጋምቤላ ክልል ጊሎ ወንዝ፣ ባሮ ወንዝ እና በንወር ዞን በሚገኙ የክረምት ደራሽ ወንዞች ሞልተዉ መስመር ጥሰው ስለፈሰሱ ቁጥሩ በውል ያልታወቀ ሕዝብ መፈናቀሉን ኢዜማ ጠቅሷል። በአኙዋ ዞን ጆር ወረዳ እና በኑወር ዞን ላሬ ወረዳ ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን ያመላከተው ኢዜማ፣ በጆር ወረዳ ብቻ ከሚገኙ ከ15 ቀበሌ ግማሽ ያህሉ ላይ ጉዳት መድረሱን ገልጿል።

በአማራ ክልልም በቅርብ ቀናት በጣለዉ ከባድ ዝናብ ጣና ሀይቅ ዙሪያ ባሉ ወረዳውች በተለይም በፎገራ ወረዳ ከፍተኛ የውሀ መጥለቅለቅ በመከሰቱ ከ 10,000 ዜጎች መፈናቀላቸውንና በሰብል እና በእንስሳት ላይ ከባድ ጉዳት መድረሱን ፓርቲው ገልጿል። በደቡብ ክልል ስር የሚገኙት ስልጢ እና ጎፋ ዞኖች የጎርፍ አደጋ መከሰቱንና በአንድ አንድ ቦታዎች ላይ ከፍተኛ ዝናብ ባስከተለው የመሬት መንሸራተት አደጋ በሰው እና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን መግለጫው አመላክቷል።

መላው ኢትዮጵያዊያን፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብም አደጋዎችን ለመከላከል፣ የሚያስከትሉትን ጉዳት ለመቀነስ እንዲሁም ተጎጂዎችን መልሶ ለማቋቋም በሚደረገው ጥረት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በመግለጫው የአደራ ጥሪ አቅርቧል። ኢዜማ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተጎጂዎችን ለማገዝ የሚውል 150,000 የኢትዮጵያ ብር በአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን በኩል ለመስጠት መወሰኑንም ገልጿል።

# ኢዜማ፣ በያዝነው ዓመት ይካሄዳል ተብሎ በሚጠበቀው ምርጫ ከ500 በላይ በሚሆኑ የምርጫ ወረዳዎች ለመወዳደር ዝግጅት እያደረገ እንዳለ አስታወቀ

መስከረም6 ቀን 2013ዓ.ም (የዜናች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የምርጫ ስትራቴጂክና ማኔጅመንት ኮሚቴ በያዝነው ዓመት ለሚካሄደው ምርጫ ዝግጅት እያደረገ እንዳለ ለዜጎች መድረክ ገለፀ ::

ኮሚቴው ባሳለፍነው የ2012 ዓ.ም ጥቅምት ወር የምርጫን ዝግጅትና ዘመቻ በሚመለከት ሰነድ በማዘጋጀት በፓርቲው የተለያዩ የኃላፊነት ቦታ የሚሰሩ፣ በምርጫው ዝግጅትና ዘመቻ ሊረዱ የሚችሉ አባላትን ያካተተ የጋራ ግንዛቤ መነሻ ፕሮግራም በመቅረፅ የምርጫ ዝግጅትና ዘመቻ ሂደት ውስጥ ገብቶ እንደነበር በማስታወስ በያዝነው ዓመት ይካሄዳል ተብሎ ለሚጠበቀው ምርጫ ዝግጅት እያደረገ እንዳለ ለዜጎች መድረክ አስረድቷል፡፡ ምርጫው ሊደረግ ይችላል ተብሎ የተገመተበትን ጊዜ ታሳቢ በማድረግ፣ ቀደም ሲል አዘጋጅቶት የነበረውን እቅድና በጀት በመከለስ ለብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ቀርቦ እንዲፀድቅ ማድረጉን ኮሚቴው ጠቁሟል፡፡

በአሁኑ ወቅትም የምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴ የፀደቀውን እቅዶች ተግባራዊ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ገልጾ ከየዘርፎቹ በየሳምንቱ የሥራ ክንውን ዘገባ በማዳመጥ በጊዜው መከናውን ያለባቸውን ተግባራት በሚፈለገው ደረጃና ወቅት መከናወናቸውን እያረጋገጠ እንዳለ አስታውቋል፡፡ በተጨማሪም በምርጫ ዞኖች በተከፋፈሉ የምርጫ ወረዳዎች የሚያደርገውን ዝግጅትና ዘመቻ በበላይነት፣ የሚያስተባብሩ አባላት ሥራቸውን በብቃት እንዲወጡ የሚያስችል የሥልጠና ፕሮግራም በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ የገለፀው ኮሚቴው፣ ፕሮግራሙ በአጠቃላይ የኢዜማን የምርጫ ዝግጅትና ዘመቻ ተግባራት እንዴት እየተከናውኑ እንዳሉ ሰልጣኞቹ ሊኖራቸው የሚገባውን ግንዛቤና በምርጫ ወረዳዎች ደረጃ የሚደረገውን ዝግጅትና ዘመቻ በምን መልኩ ለማከናውን እንደታሰበ በአግባቡ እንዲረዱና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ታስቦ እየተዘጋጀ እንዳለ ጠቁሟል፡፡

ኢዜማ በመጪው ሀገራዊና ክልላዊ ምርጫ በሁሉም ክልሎች፣ መስተዳደሮችና ከ500 በላይ በሚሆኑ የምርጫ ወረዳዎች ለመወዳደር ዝግጅት እያደረገ ነው ያለው የኢዜማ ስትራቴጂክና ማኔጅመንት ኮሚቴ፣ ኢዜማ በምርጫው ውጤታማ ሆኖ ለመውጣት፣ ምርጫው በተረጋጋ ሀገራዊ ሁኔታ እንዲደረግ የተቻለውን ሁሉ እያደረገ ይገኛል ብሏል፡፡ ምርጫው የተፈለገውን ውጤት እንዲያመጣ በአሁኑ ወቅት በፓርቲው ከምርጫ ወረዳ ጀምሮ እስከ ከፍተኛው የፓርቲው አካል ድረስ የሚደረገው ዝግጅት ብቻውን በቂ አይደለም ያለው ኮሚቴው፣ በየትኛውም የሀገሪቱ አካባቢ የሚገኙ ዜጎች ኢዜማን በመቀላቀልም ሆነ በመደገፍ ዜጋዊ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ጥሪውን አስተላልፏል ::





# የኢዜማ የምርጫ ዝግጅትና ዘመቻ በወፍ በረር

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ባሳለፍነው የ2012 ዓ.ም ጥቅምት ወር የምርጫን ዝግጅትና ዘመቻ በሚመለከት ሰነድ በማዘጋጀት በፓርቲው የተለያዩ የኃላፊነት ቦታ የሚሰሩ፣ በምርጫው ዝግጅትና ዘመቻ ሊረዱ የሚችሉ አባላትን ያካተተ የጋራ ግንዛቤ መነሻ ፕሮግራም በመቅረፅ ነበር፤ የምርጫ ዝግጅትና ዘመቻ ሂደት ውስጥ የገባው። በማስከተልም በፓርቲው መሪ የሚመራ በሥሩ ሰባት ዘርፍ ያሉት ኮሚቴ በማቋቋም የፓርቲውን የምርጫ ዝግጅትና ዘመቻ በበላይነት የሚያስተባብር የምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት የሚባል ቡድን አቋቁሟል። የዘርፉ ኮሚቴዎች፣ እጩዎች ምልመላ፣ መንግስታዊ ጉዳዮች፣ ፖሊሲና ማኒፌስቶ፣ የምርጫ የሕዝብ ግንኙነት ዘርፍ፣ የምርጫ የድርጅት ጉዳይ ዘርፍ፣ የምርጫ የግብአት አሰባሰቢና የምርጫ ጽ/ቤት፣ በሚባል የሚታወቁ ናቸው።

ዘርፎቹ ፓርቲው ማድረግ ካለበት የምርጫ ዝግጅትና ዘመቻ አንጻር የሚጠበቅባቸውን ተግባራት በብቃት ለማከናወን የሚያስፈልጋቸውን የሰው ሀይል ካሰባሰቡ በኋላ በሕዳር ወር 2012 ዓ.ም ሥራ ጀምረዋል። በዚያን ወቅት ፓርቲው የምርጫ ዝግጅትና ዘመቻን በሚመለከት ምርጫ ቦርድ አውጥቶት የነበረውን የጊዜ ሰሌዳ ታሳቢ በማድረግ ነበር የምርጫውን እንቅስቃሴ የጀመረው። የኮሮና ወረርሽኝን ምክንያት በማድረግ ምርጫው ሲራዘምና መንግሥት ባወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምክንያት የምርጫ ዝግጅትና ዘመቻውን ቀደም ተብሎ በታሰበው ሁኔታ ለማካሄድ አልተቻለም።

የኮሮና ወረርሽኝን ተከትሎ መንግሥት ያወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የማይጣረሱ ከምርጫው ጋር የተያያዙ አንዳንድ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ እነዚህ ተግባራት በዋነኛነት ያተኮሩት ለምርጫ በሚያስፈልጉ በርካታ ሰነዶች ላይ ነው። ኮሚቴው ምርጫው ሊደረግ ይችላል ተብሎ የተገመተበትን ጊዜ ታሳቢ በማድረግ፣ ቀደም ሲል አዘጋጅቶት የነበረውን እቅድና በጀት በመከለስ ለብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ቀርቦ እንዲጽድቅ አስደርጓል።

በአሁኑ ውቅት የምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴ የጸደቀውን እቅዶች ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። በዚህም መሰረት ከየዘርፎቹ በየሳምንቱ የሥራ ክንውን ዘገባ በማዳመጥ በጊዜው መከናውን ያለባቸውን ተግባራት በሚፈለገው ደረጃና ወቅት መከናወናቸውን ያረጋግጣል። ችግር የገጠማቸውን ክንውኖች አስፈላጊውን እርዳታ በማድረግ እንዲጠናቀቁ በማድረግ ላይ ይገኛል። በዚህ እቅድ ላይ ከተመሰረቱ ክንውኖች መሀል፣ የፓርቲው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ብሔራዊ ደህንነት ጉዳዮች ምን እንደሆኑ፣ መፍትሄያቸው ምን እንደሆነ፣ መፍትሄዎቹን ተግባራዊ ለማድረግ ሊገጥሙ የሚችሉትን ተግዳሮቶች እንዴት መወጣት እንደሚቻል፣ የሚያሳይ መጠነኛ መፅሀፍ በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል። መጽሀፉ፣ ኢዜማ ለሀገራችን መሰረታዊ ችግሮች ያለውን መፍትሄ የሚያሳይ ብቻ ሳትሆን፣ ኢዜማ የመፍትሄ ሀሳቦቹን ተግባራዊ ለማድረግ እያደረገ ያለውን ድርጅታዊና ሀገራዊ ዝግጅትም ያካተተ ነው፡፡

ከዚህ ተግባር በተጨማሪ በምርጫ ዞኖች በሚባል በተከፋፈሉ የምርጫ ወረዳዎች የሚያደርገውን ዝግጅትና ዘመቻ በበላይነት፣ የሚያስተባብሩ አባላት ሥራቸውን በብቃት እንዲወጡ የሚያስችል የሥልጠና ፕሮግራም በዝግጅት ላይ ይገኛል። ፕሮግራሙ በአጠቃላይ የኢዜማን የምርጫ ዝግጅትና ዘመቻ ተግባራት እንዴት እየተከናውኑ እንዳሉ ሰልጣኞቹ ሊኖራቸው የሚገባውን ግንዛቤና በምርጫ ወረዳዎች ደረጃ የሚደረገውን ዝግጅትና ዘመቻ በምን መልኩ ለማከናውን እንደታሰበ በአግባቡ እንዲረዱና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

ኢዜማ በመጪው ሀገራዊና ክልላዊ ምርጫ በሁሉም ክልሎች፣ መስተዳደሮችና ከ500 በላይ በሚሆኑ የምርጫ ወረዳዎች ለመወዳደር ዝግጅት እያደረገ ነው። ኢዜማ በምርጫው ውጤታማ ሆኖ ለመውጣት፣ ምርጫው በተረጋጋ ሀገራዊ ሁኔታ መደረግ እንዳለበት ያምናል። በዚህም ረገድ የተቻለውን ሁሉ እያደረገ ይገኛል። በፓርቲው በኩል ደግሞ ሌሎች ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው፣ በምርጫ ወረዳ የሚያቀርባቸው እጩዎችን የብቃትና የሕዝብ ተቀባይነት ደረጃ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑ ይረዳል። ይህንንም ጉዳይ በምርጫ የእጩዎች ዘርፍ በኩል አስፈላጊው ትኩረት እንዲሰጠው እያደረገ ይገኛል። በሌላ በኩል የኢዜማ የምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴ የእቅድ በጀት ላይ ምርጫውን በሚመለከት የሚያስፈልገው ወጪ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር እንደሆነ ለማየት ተችሏል። ኢዜማ ይሄን ከፍተኛ ወጪ ለመሸፈን ቀላል ባይሆንም ምርጫው ካለው ከፍተኛ ሀገራዊና ታሪካዊ ፋይዳ አንጻር፣ የግድ መሸፈን ስላለበት የተለያዩ የገቢ ምንጮችን በመጠቀም የገንዘብም ሆነ የሌሎች ግብአቶችን ለማሰባሰብ የተቋቋመው ዘርፍ አስፈላጊውን ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል።

በመጨረሻም ኢዜማ ሀገራችን ያለችበትን ወሳኝ ወቅት ታሳቢ በማድረግ፣ መጪው ምርጫ ያለው ሀገርን የማሻገርና የማረጋጋት ታሪካዊ ትርጉም ከግምት በመውሰድ፣ በምርጫ ዝግጅትና ዘመቻ የሚቻለውን ሁሉ ለማድረግ እየሞከረ ይገኛል። ይህ ምርጫ የተፈለገውን ውጤት እንዲያመጣ በአሁኑ ወቅት በፓርቲው ከምርጫ ወረዳ ጀምሮ እስከ ከፍተኛው የፓርቲው አካል ድረስ የሚደረገው ዝግጅት ብቻውን ስለማይበቃ፣ በየትኛውም የሀገራችን አካባቢ የምትገኙ ዜጎች ኢዜማን በመቀላቀልም ሆነ በመደገፍ በሚቻላችሁ ሁሉ ዜጋዊ አስተዋጽኦ እንድታደርጉ በዚህ አጋጣሚ ኢዜማ ጥሪውን ለማስተላለፍ ይወዳል።